# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) 10ኛ መደበኛ ጉባዔውን በተሳከ ሁኔታ አጠናቀቀ

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ሚያዝያ 1 እና 2 ቀን 2014 ዓ. ም በአዲስ አበባ ራስ ሆቴል አዳራሽ 10ኛ ጠቅላላ ጉባዔውን አካሂዶ በተሳካ ሁኔታ አጠናቅቋል፡፡ በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ላይ ሰፊ ውይይት ያካሄደው ጉባዔ አንኳር አንኳር በሆኑ ጉዳዮች ላይ ውሳኔዎችንም አስተላልፏል፡፡

ጉባዔው በፓርቲው ቋሚ ኮሚቴ በኩል የቀረበለትን የድርጅቱን ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ አዳምጦ ከመረመረ በኋላ መስተካከል የሚገባቸውን አስተካክሎ የፓርቲው እንቅስቃሴ ተጠናክሮ እንዲቀጥል መመሪያ ሰጥቷል፡፡ ማሻሻያ ተደርጎበት የቀረበውን የሕገ ፓርቲውን ረቂቅ መርምሮና ተጨማሪ ማሻሻያዎችን አድርጎ አፅድቋል፡፡ በመጨረሻም ድርጅቱን ለሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት የሚመሩትን አባላት በሚስጥራዊ የድምፅ አሰጣጥ ሥርዓት መርጧል፡፡ በዚህም መሠረት የፓርቲውን የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላትን፣ የአባላት መብት አስጠባቂ ኮሚሽን አባላትን፣ የውስጥ ኦዲተሮችንና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን መርጧል፡፡ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት በመሆን የተመረጡት 1ኛ) ረዳት ፕሮፌሰር ዝናቡ አበራ ሊቀመንበር፣ 2ኛ) መጋቢ ብሉይ አብርሃም ሃይማኖት ተቀዳሚ ም/ሊቀመንበር፣ 3ኛ) አቶ ገብረወልድ ወልደሰንበት ም/ሊቀመንበር፣ 4ኛ) ወ/ት ደስታ ጥላሁን ፀሐፊ፣ 5ኛ) ወ/ት ዘነበች ጤናው የፋይናንስና የንብረት ክፍል ሃላፊ፣ 6ኛ) አቶ ሸዋፈራው ሽታሁን የሕዝብ ግንኙነት ክፍል ሃላፊ እንዲሁም አቶ አንቂቦ ለማጎ፣ አቶ መላከ ካሣና አቶ ጌታነህ ዓለሙ ተጨማሪ አባላት ሆነው ተመርጠዋል፡፡

አሥረኛው የኢሕአፓ ጉባዔ አገራችን ከበፊት ጊዜ ጀምሮ ያለፈችበትን ሁኔታዎች መርምሯል፡፡ በዚህም መሠረት ታሪክን፣ ሥነ መንግሥትንና የነፃነት ትግልን ለዓለም ካስተማሩት ጥንታዊ አገራት መካከል አንዷ ኢትዮጵያ እንደሆነች፣ ለዓለም ጥቁር ሕዝቦች የነፃነትን ችቦ በአድዋ ድሏ አማካኝነት ያቀበለች አገር መሆኗን፣ የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን የማዕዘን ድንጋይ ያስቀመጠችና የፓን አፍሪካኒዝም አቀንቃኝ አገር እንደሆነች፣ በቅኝ ግዛት ሥር የነበሩ የአፍሪካ አገራት ለነፃነት ያደርጉትን ትግል ትግሌ ነው በማለት ባላት አቅም ሁሉ ያለማመንታት ድጋፍ የሰጠች አገር ኢትዮጵያ እንደሆነች ጉባዔው አረጋጧል፡፡ ኢትዮጵያ ከላይ የተጠቀሱን ሁሉ እየከወነች ለዘመናት የዘለቀች አገር ብትሆንም ዜጎቿ ዛሬም ድረስ በዴሞክራሲና በሰላም እጦት፣ በሕግ የበላይነት አለመስፈን፣ በውኃ ላይ ተቀምጣ ዜጎቿ በውኃ ጥማትና በረሃብ የሚሰቃዩባት አገር መሆኗ ኢሕአፓን እጅግ ያሳስበዋል፣ ያስቆጨዋልም፡፡

ስልክ / Phone: +251 911 400 982 ኢሜይል / email: eprp-@eprp-ihapa.com

ኢሕአፓ እንደ ፖለቲካ ድርጅት ሲቋቋም ጀምሮ ይዟቸው የተነሳቸው የፖለቲካ፣ የኤኮኖሚና የማኅበራዊ ጥያቄዎች ከ50 ዓመት በኋላም መፍትሄ ሰጭ መንግሥት አጥተውና ተባብሰው መገኘታቸው ጉባዔተኛውን እጅግ ያሳዘነው መሆኑን ስንገልጽ በታላቅ ፀፀት ነው፡፡

ህወሓት 1983 ዓ ም ጀምሮ በሥልጣን በቆየበት ጊዜ ውስጥ የሕዝቡን ወንድማማችነትና እህትማማችነት፣ የአገሪቷን የግዛት አንድነትና ሉዓላዊነት ሲሸረሽርና ኅልውናዋ አጠራጣሪ ደረጃ እስኪደርስ ድረስ እኩይ ተግባሩን ሲያራምድ እንደነበረ ጉባዔው በቁጭት ተገንዝቦታል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ የተጫነበትን ግፍና ሰቆቃ ከራሱ ላይ ለማስወገድ የማያቋርጥ ትግል በማድረግ ህወሓትን ከመንበረ-ሥልጣኑ በማስወገድ አዲስ ምዕራፍ የከፈተ መሆኑንም ጉባዔው አረጋግጧል፡፡

ህወሓት ያራምደው የነበረውን ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ የተከተላቸው እኩይ የአሠራር ዘዴዎች ህወሓት ከሥልጣን ከተወገደ ከሦስት ዓመታት በኋላም እስከ አሁን ድረስ ከአገሪቱ ያልተነቀሉ መሆናቸውን ጉባዔው አረጋግጧል፡፡ ህወሓት የትግራይን ክልል ምሽጉ አድርጎ ኢትዮጵያን ለማጥፋት ሰይጣናዊ ተግባሩን እንደቀጠለበትና በዚህ እኩይ ተግባሩ አገራችንን ለአሰቃቂና አረመኒያዊ የእርስ በርስ ጦርነት እንደዳረጋትና በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ሕይወታቸውን ማጣታቸውን፣ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ መፈናቀላቸውን፣ ቁጥራቸው በወግ የማይታወቁ እጅግ በርካታ እናቶቻችንና እህቶቻችን መደፈራቸውንና መጠነ-ሰፊ ንብረትና ተቋማት መውደማቸውንም ጉባዔው ግንዛቤ ውስዷል፡፡

ጉባዔው ይህን ሃቅ ከተገነዘበ በኋላ፦

1. ህወሓት የሚባለው እኩይ ድርጅት እስካለ ድረስ ሕዝባችንና አገራችን ሰላም እንደማይኖራቸው፣
2. በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥትም በአገሪቱ ውስጥ ሰላም ለማስፈንና የአገሪቱን የግዛት አንድነት ለማስከበር፣ ተገቢ የሆኑ እርምጃዎችን በመውሰድ ህወሓትን ከአፋር፣ ከአማራና ሌሎች ክልሎች ማስወጣት እንዲሁም ኦነግ ሸኔና ሌሎች የአገሪቱን የግዛት አንድነት የሚጻረሩ ኃይሎችንም ተገቢ እርምጃ በመውሰድ ሰላም እንዲሰፍን ማድረግ እንዳለበት አምኗል፡፡

በአገራችን ውስጥ የሰፈነው የፖለቲካ ቀውስ አገሪቱን ወዳልተፈለገ ጠርዝ ሊወስዳት እንደሚችል ጉባዔው ያምናል፡፡ ህወሓት እስካሁኗ ሰዓት ድረስ በአማራና በአፋር ክልሎች በኩል መግደልና መዝረፉ፣ የጦርነት ነጋሪት መጎሰሙን ሳያቆም በመንግሥት በኩል "በተናጠል ተኩስ አቁሚያለሁ" የሚለው ውሳኔ ኅብረተሰቡን በተለይም ተጎጂውን ሕዝብ ግራ ያጋባው መሆኑን ጉባዔው ተገንዝቧል፡፡ በመሆኑም ካለፈው ምንም እንዳልተማርን በማመን አሁንስ ምን ይከተል ይሆን? የሚል ጥያቄ በጉባዔተኞች እንዲነሳ ሆኗል፡፡

በቤኒሻንጉል ክልል የመንግሥት ፀጥታ አስከባሪዎች ሰውን ከነሕይወቱ ማቃጠላቸው እየታወቀ መንግሥት ይህን ወንጀል በፈጸሙ ግለሰቦችና ቡድኖች ላይ እርምጃ ለመውሰድ ያልቻለው

ለምን ይሆን? በሚል ጉባዔተኞች አንስተው ከመወያየታቸው በላይ ይህ ዓይነት የሕግ ጥሰትና የዜጎችን በሰላም ባሻቸው የአገሪቱ አካባቢ የመኖር መብት መግፈፍ የሚያስከትለው ቀውስ የአገሪቱን ሰላም የሚፃረርና ኅልውናዋንም አደጋ ላይ እንደሚጥል ጉባዔው አምኗል፡፡ መንግሥት “ሌቦችና ጉቦኞች የፓርቲዬ አባሎች ናቸው” እያለ ለምን እርምጃ እንደማይወስድ ጉባዔተኛው ሊረዳው አልቻለም፡፡

ኦነግ ሸኔ በኦሮሚያና አጎራባች ክልሎች ብዙ ከተሞችን እየተቆጣጠረ መሆኑን የኦሮሚያ ክልል መንግሥት በይፋ ያመነው ጉዳይ ነው፡፡ ይሁንና የኦሮሚያ ክልል በልዩ ኃይልና በሚሊሺያ ቁጥር ከሌሎች ክልሎች ቁጥር የበለጠ መሆኑ እየታወቀ እንዴት ኦነግ ሸኔን ሊቆጣጠር አልቻለም? የሞጆ አካባቢ ነዋሪዎች “ባለሥልጣኖች ኦነግ ሸኔ በመሆናችሁ እኛን አስፈጃችሁን” ሲሉ የተደመጠው እውነትነት አለው እንድንል አድርጎናል፡፡

ጉባዔው በከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘውን የሥራ አጥነት ሁኔታም በሚገባ መርምሯል፡፡ የሥራ አጡ ቁጥር በየጊዜው መጨመሩ የጠም አዳሪውን ቤተሰብ ቁጥር ከዓመት ወደ ዓመት እያሳደገው መሆኑን ጉባዔው ተገንዝቧል፡፡ ይህ ሁኔታ በአስቸኳይ ካልተገታ በረሃብ የተጎዳ ኅብረተሰብ አገሪቱን ወደ ከፍተኛ ቀውስ ውስጥ ሊያስገባት እንደሚችልም ጉባዔው አምኖ ችግሩን ለመቅረፍ በመንግሥት በኩል እየተወሰደ ያለው እርምጃ አጥጋቢ አለመሆኑን ጉባዔው ተገንዝቧል፡፡

የኢሕአፓ አሥረኛ ጉባዔ የአገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ በጥልቀት መረምሮ ሰፊ ውይይት ካካሄደ በኋላ የሚከተሉትን ውሳኔዎች አስተላልፏል፡፡

1ኛ) ህወሓት በኃይል የያዛቸው ቦታዎች ነፃ ወጥተው ተፈናቃዮችም ወደ ቀዬያቸው እንዲመለሱና መንግሥት በቂ የመቋቋሚያ ድጋፍ እንዲያደርግላቸው፣

2ኛ) ህወሓትና ኦነግ ሻኔ እስካሁንም ድረስ ሕዝብ እየገደሉ ንብረት እየዘረፉና እያፈናቀሉ በመሆናቸው የሕዝብን ሰላምና ደህንነት ለማስከበር መንግሥት በአስቸኳይ መፍትሄ እንዲሰጥ፣

3ኛ) በሰው ሠራሽና በተፈጥሮ ችግር ምክንያት የተከሰተውንና እየተስፋፋ ያለውን ድርቅና ረሃብ ለማስወገድ ችግሩ በጣም ጎልቶ በተከሰተባቸው አካባቢዎች መንግሥት በአስቸኳይ ዜጎቹን ለመታደግ አስፈላጊውን የምግብና የውኃ አቅርቦት ማሟላት እንዳለበት፣ ኢሕአፓም በሶማሌ ክልል እንዳደረገው ሁሉ የድርሻውን ለመወጣት ዝግጅ መሆኑን፣

4ኛ) የዋጋ ግሽበትን ለመቆጣጠር በአገር ውስጥ የሚመረቱትንም ሆነ መንግሥት ከውጭ በሚያስገባቸው መሠረታዊ ሸቀጦች ስርጭት ላይ ልዩ ቁጥጥር በማድረግ ለዜጎች ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑ መሠረታዊ ሸቀጦች አቅርቦት መሻሻል እንደሚገባቸው፣

5ኛ) የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ተፈታኞች ውጤት፣ በተለይም በአማራ ክልል የታየውን ከፍተኛ ችግር በማጣራት የተፈታኞቹ ሁሉ ትክክለኛ ውጤት በአስቸኳይ እንዲገለጽ፣

6ኛ) በኦሮሚያ ክልል በአማርኛ ተናጋሪዎች ላይ የሚደረገውን ማፈናቀልና ግድያ መንግሥት በፍጥነት እንዲያስቆምና የፀጥታ ዋስትና ለሕዝብ እንዲሰጥ፣

7ኛ) የግል ባለ ሀብቶች በአገራችን ውስጥ ማዋዕለ ነዋይ በማፍሰስ በኤኮኖሚ ውስጥ ሙሉ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ለማድረግ መንግሥት ባለሃብቶች የውጪ ምንዛሪ በቀላሉ የሚያገኙበትን፣ የብድር አገልግሎት የሚመቻችበትን፣ የመሬትና የቴክኒክ አገልግሎት የሚስፋፋበትን ሁኔታ በመቀየስ በግብርናና ኢንዱስትሪ ላይ እንዲሰማሩ ልዩ አቅጣጫ እንዲያስቀመጥ፣

8ኛ) በዓለም አቀፍ ዲፕሎማሲ ረገድ የኢትዮጵያን ጥቅሞች ለማስጠበቅ የሚችሉ በሞያው ብቃት ያላቸውን ኢትዮጵያውያን በትክክለኛ ቦታ ላይ ማስቀመጥ እንደሚያስፈልግ፣

9ኛ) ሕዝባችን በመልካም አስተዳደር እጦትና በሙስና መማረሩን በተደጋጋሚ የገለጸ በመሆኑ መንግሥት በዚህ እኩይ ድርጊት ላይ የተዘፈቁትን እየመነጠረ አስቸኳይ እርምጃ እንዲወስድና ለሕዝቡም ይፋ እንዲያደርግ፣

10ኛ) በመንግሥት ሹማምንትና በባለ ሀብቶች መካከል ያለው የጥቅም ትስስር ለደሃው የኅብረተሰብ ክፍል የሚገባውን ፍትኀዊ የሀብት ክፍፍልና በአጠቃላይ ፍትኅን የሚጎዳ በመሆኑ ይህ የጥቅም ትስስር በአስቸኳይ እንዲፈርስ መንግሥት ልዩ ትኩረት ሰጥቶት እንዲሠራ፣

11ኛ) ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ሕጎች የአገር ውስጥ ሕጎች አካል በመሆናቸው የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ድንጋጌ አንቀጽ 2 ከኢፌድሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 25 ጋር መሳ ለመሳ በሥራ ላይ እንዲውል፣

12ኛ) በጠራራ ፀሐይ በቤንሻንጉል ክልል የሰው ልጆችን ከነሕይወታቸው በእሳት ያቃጠሉ የመንግሥት አካላት በአስቸኳይ ለፍርድ እንዲቀርቡ፣

13ኛ) በአገራችን ውስጥ ያሉትን ችግሮች ለመፍታት ሰላም፣ ብሄራዊ ዕርቅና መግባባት እጅግ አስፈላጊ በመሆናቸው በቅርቡ የተቋቋመው የብሄራዊ መግባባት ኮሚሽን ከፍተኛ ሚና ሊጫወት እንደሚችል በማመን ኮሚሽኑ ሥራውን በገለልተኝነት እንዲያከናውን መንግሥት ተጽዕኖ እንዳያደርግበት እንዲሁም ኮሚሽኑ ለሥራው የሚያስፈውን ሁሉ በማቅረብ መንግሥት አስፈላጊውን ትብብር እንዲያደርግለት፣

14ኛ) የኢሕአፓ 10ኛ ጉባዔ አሁን በአገራችን ውስጥ ለተቀፈቀፉት ችግሮች ሁሉ ምንጩ ህወሓት ከፋፍሎ ለመግዛት እንዲያመቸው የቀረጸውና አገራችን የምትተዳደርበት ሕገ መንግሥት ነው ብሎ ያምናል፡፡ መንግሥትም ይንን ሃቅ ተቀብሎ ሕገ መንግሥቱ በሕዝቡ ሙሉ ተሳትፎ የሚሻሻልበትን መንገድ እንዲያመቻች፣

15ኛ) የተፎካካሪ ፓሪቲዎች አገራችን ላይ የተጋረጠውን አደጋ ለመቀልበስ አንድነታችንን አጠንክረንና በኅብረት ቆመን የተጠናከረ ትግል ማድረግ እንደሚገባ በማመን ጉባዔው ለተፎካካሪ ፓርቲዎች ጥሪውን እያቀረበ የኢሕአፓ የአመራር አባላትም የጋራ ትግሉን አጠናክረው እንዲቀጥሉ መመሪያ ሰጥቷል፡፡

ሚያዝያ ፫ ቀን ፪ ሺህ ፲፩ ዓ. ም